# የተሻለ ፓርቲ እስኪመጣ የኢህአዴግ ደጋፊ ነኝ

አንዳርጋቸው ፅጌ <መለስ ዜናዊ ህግ በሆነበት ሀገር..> የሚል ፅሁፍ በቅርቡ በኢንተርኔት በትኗል:: የጠቀሳቸው <የቆሌ ; የአድባር እና የእድል> ቃላቶች ልብ እያልን የፅሁፉን መነሻም መድረሻም እንመርምር::

ግንቦት7 ለሚራገቡ አሉባልታዎች ማብራሪያ ለመስጠት ጊዜም ፍላጎትም እንደሌለው አስረድቶናል:: ሆኖም ግን በአሜሪካ ፖለቲካ እያንዳንድዋ አሉባልታ ተራግባ ምን አይነት ጉዳት እንደምታደርስ በ2008 የፕሬዚዳንታዊ እጩነት ውድድር ዙሪያ ተረድተናል:: በኦባማ ዙሪያ የተነዙ እና የሚነሱ አሉባልታዎችን ለመመከት ዌብሳይት እና ቡድን እስከማቋቋም የተደረሰው የአሉባልታዎችን ጡንቸኛነትን በመረዳት ነው::

ኢህአዴግም ልክ እንደ ግንቦት ሰባት ለአሉባልታዎች ጊዜ የለንም በሚል ፈሊጥ የኢትዮ-ሱዳን የድንበር መካለል እውነት ይሁን ውሸት በደንብ ግልፅ አድርጎ ለህዝብ ማስረዳት አልፈቀደም ወይም አልቻለም:: የመንግስት ሚዲያዎች እንደ በቂ ማስረጃነት የሚጠቀሙት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለፓርላማው የሰጡትን ማብራሪያ ነው:: አሜሪካን ሀገር ከሚኖሩ የግለሰብ ድህረ ገፆች ባነሰ ስለ <አሉባልታው> ህዝብን ማሳወቅ ያልቻለ ደካማ ማስታወቂያ ሚንስትር ነው ኢህአዴግ ያለው::

ወደ ግንቦት 7 ንቅናቄ ስንመ ህዝብን አገለግላለሁ ; ለህዝብ ነው የምታገለው ; ለመሞትም ዝግጁ የሆንኩት ; ብሎ ህዝብን አለማንቃት ; አለማስተማር ; ሲሳሳት ደግሞም ሳይታክቱ ለማስረዳት አለመሞከር ለህዝብ ታግያለሁ አያስብልም:: ትግል ዘርፈ ብዙ ነው:: <ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው> አባባል የወሬን ጡንቸኛነት የሚመሰክር ነው:: በተጨማሪም የሚነዙ እውነታ ያላቸው ወይም የሌላቸው ወሬዎችን <የወያኔዎች> ; የሚተቸን ደግሞም <ወያኔ> ማለት ከኢህአዴግ ስም-ለጣፊ ባህሪ ፈቅ ያላለ አመል ነው:: ለአብነት ያህል ሪፖርተር ጋዜጣን ብንወስድ ጋዜጣውን የ<ወያኔ> ማለት የተሳሳተ ነው:: ብርሀኑ ነጋ (ዶ/ር) በ<የነፃነት ጎህ ሲቀድ> መፅሀፉ ከአማረ አረጋዊ እና ከሪፖርተር ጋር ጥሩ የሚባል ግንኙነት እንደነበራቸው ግልፆ እና ሪፖርተርንም የሚያከብረው ጋዜጣ እንደነበረ ነግሮን ከፓርላማ ገቡ እና አትግቡ ንትርክ ጊዜ በኃላ ግን የነበረው ክብር እና ግንኙነት እንደወረደ ነግሮናል:: ከዚያም አልፎ አሁን ጋዜጣውን <ወያኔ> እስከማለት ደርሷል:: ለእኔ ሪፖርተር ጋዜጣ በጋዜጣዊ ስነ-ምግባር የታነፀ ሙያዊ ክህሎትን የተላበሰ ጋዜጣ ነው:: ላለፉት አራት አመታት ወይም ከዚያ በላይ ባለፈው ወር የፀደቀውን የፕሬስ ህግ እንዳይፀድቅ ሲታገል የነበረ ; በረከት ስምኦንም ከመደብደብ ያላነሰ ንትርክ የገጠመ ሰውዬን <ወያኔ> ማለት ለራስ ህሊና አለመታመን እና እውነታን መካድ ነው::

በግንቦት 7 ላይ የሚሰነዘሩ ጥያቄዎች ; ትችቶች ; ከግራ መጋባት እና የድርጅቱን ትክክለኛ አላማ ባለማወቅ የሚቀርቡ መጣጥፎችን እንደ በጎ ተቀብሎ አምለካከትን እና ብዥታን ለማጥራት ከመሞከር ይልቅ አናንቆ መተው <ጠንካራ ነኝ ; ከአምስት አመት በፊት ኢህአዴግን ከስልጣን አወርዳለሁ> ከሚል ቡድን አይጠበቅም::

ግንቦት 7 ኢህአዴግን እና የኢህአዴግ ተከታዮችን በአራት ወር ውስጥ እንቅልፍ የነሳ ድርጅት እየሆነ እንደመጣ አንዳርጋቸው በዚሁ ፅሁፉ ብገፅ ሁለት የመጀመሪያ አንቀፅ ላይ ፅፎታል:: ካለኝ መረጃ እና ከማውቀው በመነሳት ግን ቡድኑ አውሮፓ እና አሜሪካ

እየዞሩ የመንደርደሪያ ስብሰባዎችን ከማድረግ ፈቅ ያለ እንቅስቃሴ እያደረገ አይደለም:: ለሰባት ሺህ በኢትዮጵያ ለሚኖሩ ኢሜል ተጠቃሚዎች <አንብባችሁ አሰራጩ> የሚል መልእክት ያዘለውን የቡድኑን ብቃቱን ያልጠበቀ ሳምንታዊ ጋዜጣ መላክ ከሆነ እንቅልፍ ነሺው በእውነቱ አንዳርጋቸው ተሳስቷል:: የግንቦት 7 ልሳን የሆነው ሳምንታዊው ጋዜጣ ያለፉት ስምንት እትሞቹ እየተሻሻሉ ሳይሆን እየወረዱ ; ጠቃሚ እየሆኑ ሳይሆን ራሱን ቡድኑን እያሳጡት እንደሆኑ ነው የተረዳሁት:: አዲስ አበባም ጋዜጣውን በጉጉት የመጠበቅ ስሜቱን እየወረደ ነው:: ከግንቦት ሰባት ልሳን በተሻለ <ኢትዮጵያ ዛሬ> ድህረ ገፅ ተስፋ ሰጪና ሚዛናዊ ዜናን በማቅረብ ዝናን እያተረፈ እንደመጣ ነው የተረዳሁት:: ኢትዮጵያ ዜና ድህረ ገፅ በዚሁ ከቀጠለ በአጭር ጊዜ ውስጥ በተነባቢነት በኢትዮጵያ ዙሪያ ካሉ ድህረ-ገፆች ቀዳሚ እንደሚሆን አልጠራጠርም:: በዚህ አጋጣሚ የድህረ ገፁን አዘጋጆች በርቱ እላለሁ::

ስለ አምባሳደር ሳሙኤል እና ተስፋዬ ሀቢሶ በጠቀሰው ፅሁፍ ላይ የገረመኝ የተስፋዬ ሀቢሶ መኖር ነው:: የቀድሞው አምባሳደር ተስፋዬ ሀቢሶ በአሁኑ ሰአት በጡረታ ላይ ያለ እና በኢትዮጵያ የሚኖር መሆኑን አንዳርጋቸው ልብ ሊል ይገባል::

ሪፖርተር ጋዜጣ በአንዳርጋቸው ፅሁፍ ላይ ያወጣውን ትንታኔ እንደ <ድርሰት> ከመቁጠር ይልቅ በምሁራዊ አቀራረብ የሪፖርተርን የተሳሳተ ትንታኔ እራቁቱን የሚያወጣ ፅሁፍ ብናነብ እንመርጣለን::

አንዳርጋቸው ቀደም ብሎ ያወጣው <የአማራ ህዝብ ከየት ወዴት> የሚለው ፅሁፉ አሁን ባላንጣው ከሆነው ኢህአዴግ ጋር ሽርክ በሆነ ጊዜ የተፃፈ ነው:: አንዳርጋቸው ከኢህአፓ ጊዜ ጀምሮ ፓርቲ በመቀየር እና በስሜታዊነት በመነዳት የታወቀ ነው:: መጀመሪያ ኢህአፓ- ቀጥሎ ህወሀትን ለመቀላቀል መሞከር-ቀጥሎ የኢህአዴግ ከፍተኛ ባለስልጣን መሆን- ቀጥሎ የቅንጅት ድጋፍ ሰጪ መሆን-ቀጥሎ ቅንጅት መሆን- ቀጥሎ ዜግነትን መቀየር- ቀጥሎ ግንቦት ሰባት መሆን....................... እድሜ ይስጠን እንጂ የሚቀጥለውንም በቅርቡ እናይ ይሆናል::

1. ግንቦት ሰባትን ምን አመጣው?

የግንቦት ሰባት ፕሮግራሞች ብዙዎቹ በቀላሉ የሚስማሙበት እንደሆነ አንዳርጋቸው ገልፆአል:: እኔም በዚህ ላይ ጊዜዬን ላለማጥፋት ወስኛለሁ:: ምክንያቱም አብዛኛዎቹ ኢህአዴግን የሚቃወሙ ቡድኖች እና ድርጅቶች (የመገንጠል አላማ ከሌላቸው በቀር) አላማቸው አንድ እና አንድ ነው:: በብሄር ላይ የተመሰረተን ፖለቲካ አይደግፉም ; የኤርትራ መገንጠልም አይዋጥላቸውም-ቢዋጥላቸውም የአሰብ ጉዳይ ከቶ የማያጠያይቅ የኢትዮጵያ ነው:: ስለዚህ የሚለያያቸው የፖለቲካ ራእይ ሳይሆን ራእዩን የሚያስፈፅሙ ፖለቲከኞች የግል ባህሪዎች ናቸው::

2. የእንዴት እንታገል ጥያቄና ግንቦት 7

ሀ. ሰላማዊና ህጋዊ በሆነ መንገድ

ህጋዊውን እና ሰላማዊን መንገድ በማደብዘዝ ከኢህአዴግ ጋር ተጠያቂ የሚሆን ቡድን ቢኖር የታሰሩት የቅንጅት አመራሮች ናቸው:: ቡድኑ እስከመጨረሻው ያስቀመጠው ስምንት ነጥብ ካልተሟሉ ፓርላማ እንደማይገባ ካስቀመጠ በኋላ ከኢህአዴግ ጋር የተያያዘው እልህ ፖለቲካዊ ብስለት ያልነበረው ነው:: ደጋፊን በደንብ ሳያነቁ የትግል አቅጣጫውም እንቅፋቶችን በመዘርዘር መፍትሄዎችን ቀድሞ ያላስቀመጠ በስሜት እና በችኩልነት የሚነዳ ስለነበር መጨረሻው መታሰር እና ይቅርታን ጠይቆ መፈታት ሆኗል:: ኢህአዴግም የተንገራገጨውን አቅሙን አዳብሮ ሁሉን ነገር ከድጡ ወደ ማጡ አድርጎታል:: ኢህአዴግ ይህን ብታደርጉ ወዮላችሁ አለቃችሁም እያለ በድፍረት <አታድርጉ> የተባሉትን ሲያደርጉ ታሳሪዎቹ እና ይቅርታ ጠያቂዎቹ አመራሮች በደንብ መፍትሄ እና ድል የሚያመጣ እቅድ የነደፉ ይመስሉ ነበር:: ሆኖም ግን የተማመኑበት ነገር ቢኖር ከኢህአዴግ ጋር እንዲስማሙ ደጅ ሲጠኑዋቸው የነበሩ የታላላቅ መንግስታት ዲፕሎማቶች ትኩረት ማግኘትን ነው:: ኢህአዴግን ዲፕሎማቶቹ እያስፈራሩም እየተለማመጡም እኛ የምንጠቀምበትን ውሳኔ እንዲወስን ያደርጉታል የሚል መላ ምት ነበራቸው:: ከዚህም በተጨማሪ የሀያላን ሀገር ዲፕሎማቶች የኢህአዴግን መዳከም አይተው እኛን ይደግፉናል የሚል እምነትም ነበራቸው::

የተሳሳተው ቀመር ያሳሳተው ህዝብን ብቻ ሳይሆን እራሳቸው ታሳሪዎችን እና ኢህአዴግንም ነው:: እየፈካ የነበረው ዲሞክራሲ ጨለመ እየበሰለ የነበረው ፕሬስም ተዘግቶት እርፍ አለ-በጣት ከሚቆጠሩ ጋዜጦች በቀረ::

እንደ ፖለቲካ ኪሳራ የሚቆጠረው ደግሞም ይቅርታን ጠይቆ መውጣት ነው:: የውሸት ይቅርታ ጠይቀን ነው የተፈታነው- ይቅርታ ጠይቀን እንድንፈታ የፈለግነው ይቅርታ በጠየቅንበት ወረቀት ላይ ለማመፅ ነው የሚለው ከፖለቲካዊ ስነ-ምግባር አንፃር ሲታይ የንግድ (ቢዝነስ) አመክንዮ የተላበሰ ነው:: ይቅርታ ጠይቀው እንዲፈቱ ታሳሪዎች የፈለጉበት ዋነኛ ምክንያት ከእስር ቤት ውጭ ባለው አመራር እና ደጋፊ ላይ እምነት በማጣታቸው እና ከእኛ ሌላ ትግሉን ግብ የሚያደርስ ሌላ ጠንካራ ስብስብ (ግለሰብ) አይኖርም በሚል አመለካከት ነው:; አለበለዚያ የምኞት ኑሯቸው ናፍቋቸው ነው::

በፖለቲካ ታሪክ በስህተት ተወንጅሎ የታሰረ ግለሰብ የታሰረበት ጉዳይ ወንጀል መሆኑን አምኖ አሳሪውን አካል ይቅርታ ጠይቆ ከተለቀቀ በኋላ <አይ ከእስር ቤት ልወጣ ፈልጌ ነው እንጂ አለመሳሳቴን አውቃለሁ> ቢል ተቀባይነት የለውም:: ከዚህ አንፃር ታሳሪዎቹ ህሊናቸውን ሸጠው ሆነ እውነታውን ተረድተው ይቅርታ ጠይቀው ይቅርታም ሲጠይቁም ይሄን ይሄን ባደርግ <አትማረኝ> ብለው እስከወጡ ድረስ ቃላቸውን ማክበር አለባቸው::

ከዚህ አንፃር የንቅናቄው መስራቾች የኔን አመኔታ እንዳያገኙ ከሚያደርጋቸው ነገሮች አንዱ ከእስር ቤት የወጡበት መንገድ እና አሁን የሚከተሉት መንገድ ነው:: ላመኑበት መሞት ማለት ጊዜን በመግደል ከሆነ እርግጥ እኔና እነሱ መስዋእትነት ላይ ያለን አመለካከት ሳይሆን ትልቁ መስዋእትነት ምን እንደሆነ ባለን አመለካከት እንራራቃለን::

ሰላማዊ ትግሉ መች ተሞከረ እና የሚለውን የመስፍን ወልደማርያም (ፕ/ር) አመለካከት <በቅጡ መች ተሞከረ> የሚል ሀረግ ጨምሬበት እኔም እጋራዋለሁ:: ሰላማዊ ትግል የጠነከረ መስሎ የተሞከረው በግንቦት97 ምርጫ ነው:: ህዝብ ከነበረው

ብሶት እና ለለውጥ ከመጓጓት በመነሳት ድጋፉን ያሳየበት 97ምርጫ በእውነቱ ውጤቱ ጥሩ ስላልነበረ መዳከም የነበረበት ሳይሆን በተስፋ ሰጪነቱ እና በአመላካችነቱ እንደ ጅማሬ ታይቶ መቀጠል የነበረበት ነበር:: ሰላማዊ ትግል በስልጣን ላይ ያለን ፓርቲን ተንኮሎች እንዴት ማሸነፍ እንደሚቻል እና ህዝብንም ከጎኑ የሚያሰልፍ የፍቅር መንገድ ነው:: ሰላማዊ ትግል ከቂም ካልፀዳ በፍርሀት የተሞከረ እንጂ በትግሉ መንገድ ላይ ዘለቄታዊ እምነት በመያዝ የተሞከረ አያደርገውም::

በ97 ምርጫ ኢህአዴግ ስልጣን ባለመልቀቁ አሁን አሁን በተለይ እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይወዳታል ከሚሉት ወገኖች ውስጥ ራሴን ፈርጄዋለሁ:: የቀድሞው ቅንጅት ከኢህአዴግ በላይ የተለየን ሀሳብ የሚቀበሉ ሳይሆን ሀሳቡን ተቀጥያ ስም በሚሰጡ ; አመንጪውንም ከመኮርኮም በላይ ለማጥፋት ወደ ኃላ በማይሉ ሰዎች የተሞላ ነበር:: የቀድሞው ቅንጅት ከፍተኛ አመራሮች ስልጣን የተሰጣቸው ያለፈው ታሪካቸው ተጠንቶ በህብረተሰቡ ዘንድ ያላቸው ተቀባይነት ታይቶ ሳይሆን ለጊዜያዊ ፖለቲካ ትርፍ ተብሎ እና የሚሰጡት ጥቅም ታይቶ እንደነበረ አይተናል:: የቀድሞው ቅንጅት አንዴ ሳይሆን ሁለቴ ሳይሆን ደጋግሞ ከዋናውም ላይ ከስንጣቂውም ላይ የተሰነጣጠቀው ስብስቡ ላይ ሁሉም የተለያየ አጀንዳ ይዞ ስለቀረበ ነው:: ቅንጅት ፓርላማ ቢገባ ለፓርቲው ሁለት ትልቅ ፖለቲካዊ ፋይዳ ነበረው::

1. የራሱን አመራሮች እና አባሎች አጥርቶ ለማየት እንዲሁም ድክመቶችን ለማሻሻል እና ዘላለማዊ ፓርቲ እንዲሆን ሂስ እና ገለ ሂስን አመራሮቹ እንዲለምዱ የሚረዳ ፋይዳ እና

2. የመንግስት አወቃቀርን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲን እና መንግስት ቢቀያየሩም የማይቀየሩ ዘላቂ የኢትዮጵያ ችግሮች እና ጠላቶችን እንዲያቅ እናም እንዴት መቋቋም ከተቻለ ማስወገድ እንደሚቻል የሚቀይስበት አጋጣሚዎች ነበሩ::

ኢህአዴግ ለዲሞክራሲ አዲስ ነው:: የኢህአዴግ አመራሮች በተናጥልም (ህወሀት ኢህዲን ኦህዴድ) በአንድ ፓርቲ ስምም እየነበሩ ሶሻሊዝምን ከልባቸው የተቀበሉ እና ለረጅም አመታት በሶሻሊዝም መርሆች የተጓዙ ናቸው:: ኢህአዴግ ዲሞክራሲን <አብዮታዊ ዲሞክራሲ> ብሎ የተቀበለው በወቅቱ በአለም ላይ ከነበረው የሀይል ሚዛን መዛባት በኃላ ነው:: ስለዚህም ኢህአዴግ ዴሞክራሲን ኢትዮጵያ ውስጥ አሰፍናለሁ ሲል አስተማሪም ተማሪም ሆኖ ነው:: ተማሪው አስተማሪ የሚሆንበት አጋጣሚ ሲፈጠር ደግሞ አውቆ ሳይሆን ሳያውቅ ነው የተሳሳተው በሚል ለጋራ ጥቅማችን ልናግዘው ይገባል:: ሆኖም ግን በዲሞክራሲ አገር ውስጥ ለረጅም ጊዜ የኖሩ ብሎም በከፍተኛ ተቋሞቻቸው ያስተማሩ ግለሰቦች ኢ-ዲሞክራት ሆነው ስናገኛቸው <ባህር ውስጥ እየኖር የማይረጥብ አሳን> አባባልን ትክክለኝነት አምነን ልንቀበል እንገደዳለን::

የአንዳርጋቸው ብልጣ ብልጣዊ አቀራረብ ደግሞም እንዲህ ይነበባል-ገፅ 8 ሁለተኛ አንቀፅ

> *< እግረ መንገዴን ለማሳሰብ የምፈልገው ይህ ትንተና የመለስ አገዛዝን ኢላማ ያደረገ እንጂ ህጋዊና ሰላማዊ ትግል ይቻላል ያሉትን ደርጅቶችንና ግለሰቦችን ኢላማ ያደረገ አይደለም:: እኛ አይቻልም ብለን በወነው ሀገራዊ ሁኔታ ውስጥ*

*ይቻላል ብለው የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች ባምኑት መንገድ መንቀሳቀስ መብታቸው እንደሆነ እናውቃለን:: ከእዛም አልፈን ህጋዊ የሆነው ሰላማዊ ትግላቸው እንዲሳካላቸው እንመኛለን:: እነዚህ ግለሰቦችና ድርጅቶች በግላቸው ትክክል ነው የሚሉትን የትግል ስልት እንዲመርጡ እንደኛው ተጠበውና ተጨንቀው ነው ብለን እናስባለን:: ምርጫቸው እንደኛው ለሀገርና ለወገን በጎ ከማሰብ ከሚመጣ ቅን ፍላጎት የመነጨ ነው ብለን እናምናለን:: እድል አግኝተው ቢሳካላቸው ; እኛ እድል አግኝተን ቢሳካልን ለህዝብ ቃል ትየገባነውን ለመፈፀም አለን ብለን የምናስበውን ታማኝነት እነሱም አላቸው ብለን እናምናለን::>*

ከላይ የተፃፈው አባባል ከአንድነት ፓርቲ (ስሙ በምርጫ ቦርድ ተቀባይነት አላገኘም እስካሁን) ውጪ የልደቱን እና የነ በየነ ጴጥሮስ (ፕ/ር) እንደማያጠቃልል አልጠራጠርም:: ይህ አባባሉ የሚያሳየን ነገር ቢኖር ኢህአዴግም በሰላማዊም ሆነ ሰላማዊ በሆነ መንገድ እኛ ወይም <አንድነቶች> ካስወገዱት አብረን ልንሰራ ወይም ስልጣን ልንይዝ ዝግጁ ነን የሚል እንድምታ አለው:: ለኢህአዴግ ደግሞም <አንድነት> ፓርቲ የ<ግንቦት 7> ንቅናቄ ቅርንጫፍ ነው የሚል አመለካከት እንዲያድርበት መንገድ ከፋች ነው:: ከዚህ በተጨማሪም ከላይ ያለው አባባሉ አሁንም በንቅናቄው ጉዞ ስኬታማነት እርግጠኛ እንዳልሆነ ያሳየናል:: በመሰረቱ ሰላማዊ ትግልን በመረጡ እና ሰላማዊ ያልሆነ ትግልን በመረጡ መካከል ከፍተኛ የአመለካከት ልዩነት አለ:: ሰላማዊ ትግልን የመረጡ ስልጣን ሲይዙም ችግሮች ምንም ያህል ፈታኝ ቢሆኑ በሰላማዊ መንገድ እንደሚፈቱ መሰረታዊ እምነት ያሳዩ ሲሆኑ ሰላማዊ ያልሆነ ትግልን የመረጡት ደግሞም ልክ እንደ ኢህአዴግ ፈታኝ ጊዜ ሲመጣ ጡንቻቸውን እንደሚጠቀሙ አያጠራጥርም:: ከዚህ በላይ ትልቅ ልዩነት የለም:: ዛሬ በሀሳብ ልዩነት የተገኙ ሰዎችን በስድብ እና ስም በመለጠፍ የተጀመረ ባህሪ እና የትግል ስልት ነገ አቅሙ ሲፈቅድ ምን እንደሚከተል አመላካች ነው::

ግንቦት 7 ከመለስ (ኢህአዴግ ብል እመርጣለሁ-አገሪቷን መለስ ሳይሆን ኢህአዴግ ስለሚመራት) ውጪ ጠላት እንደሌለው ይነግረናል:: ልደቱ እና ፓርቲውስ? እነሱ ከተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ አይመደቡንም? ወይስ ልደቱን እንደጠላት አታዩትም? ቢያንስ <የብርሀኑ ነጋ ውጊያ የጨበጣ ነው!> የሚለው በቅርብ የሰጠው አስተያየት አላሳመማችሁም?

## <u>ሰላማዊ ባልሆነ መንገድ መታገል</u>

በሰላማዊ ትግል ላይ ማመን ክንዲሽናል መሆን የለበትም:: ፖለቲካ መሰረታዊ እምነት እና አቅጣጫዎች ከሌሉት ለስህተት እና ለንቅዘት የተዳረገ ይሆናል::

በዚህ አርእስት ላይ ያለው ትንታኔ ከፀሀፊው ቢበዛ ደግሞም የንቅናቄው ቅርብ ሰው ውጪ በግልፅ ሊረዱት የማይችል አቀራረብ ነው:: ንቅናቄው ህቡእ ከመሆኑ አንፃር ለጥንቃቄ ተብሎ የተፃፈ የሚመስለው ይህ አርእስት እርስ በራሱ የሚማታ ሀሳብ የያዘ ነው::-ገፅ 9 ሁለተኛ አንቀፅ

> *<....በስልጣን ላይ ያለው አገዛዝ በሰራቸው አሰዋሪና አሳፋሪ ስራዎች በህዝብ የተተፋ ሆኗል:: ይህ ሁኔታ ሰፊ የሆነ የህዝባዊ እምቢተኛነት የሰላማዊ እንቅስቃሴ በህቡእ ማደራጀት የሚያስችል ነው የሚል እምነት አለን:: በሌላ በኩልም ከምርጫ 97 ጋር ተያይዞ ህጋዊ በሆነ መንገድ በከፍተኛ መስዋእትነትም ቢሆን ህዝብ የተማራቸው በሰላማዊ መንገድ የመታገል ልምዶችና እውቀት አለው:: ይህንን እውቀቱንና ልምዱን እንዳለፈው ጊዜ አሱን ለጥቃት ሳያጋልጥ; ህግና ህአገ መንግስት አለ ብሎ ሳይዘናጋ በጥንቃቄና በሚስጥር በመደራጀት በስራ ላይ ማዋል ይቻላል ብለን እናምናለን:: እንዲህ አይነቱንም አደረጃጀት ለመፍጠር አቅምና ብቃቱ አለን እንላለን:: በመሆኑም የመከራ እድሜያችንን ለማሳጠር ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚኖረውን ሰላማዊ የትግል ስልት ግምት ውስጥ ያላስገባ; በአመፅ ላይ ብቻ የቆመን የትግል ስልት ልንቀበለው ፈቃደኞች አልሆንም::>*

*<የሰላማዊ እንቅስቃሴ በህቡእ ማደራጀት..... ሰላማዊ የትግል ስልት ግምት ውስጥ ያላስገባ; በአመፅ ላይ ብቻ የቆመን የትግል ስልት ልንቀበለው ፈቃደኞች አልሆንንም>* የሚለው ሀረግ እጅግ ምስጢራዊ አፃፃፍ ነው:: ሰላማዊ ከሆነ ለምን በህቡእ መደራጀት አስፈለገ? ሰላማዊ ከሆነ ለምን ንቅናቄ አስፈለገው? ሰላማዊ ከሆነስ እንዴት ብሎ ነው ከግንቦት 7 መርህ ከሆነው የ<አመፅንም ትግል ጨምሮ> ከሚለው ፕሮግራም ጋር የሚስማማው?

ሰላማዊ በሚለው ቃል ላይ እኔን እና አንዳርጋቸውን የሚያስማማን ትንታኔ ያገኘሁት በገፅ 9 የመጨረሻው አንቀፅ ላይ *<በህቡእ የሚደራጅ ሰላማዊ ትግል: ህዝብ በህገ-መንግስቱ የተቀመጡትን ህጋዊ መብቶቹን ለማስከበር የሚያደርገው ፍትሀዊ ትግል ቢሆንም...>* የሚለው ሀረግ ሰላማዊ ማለት በኢህአዴግ ህገ-መንግስት የሚገዛ እንደሆነ ያስረዳል:; እኔስ በኢህአዴግ ህገ-መንግስት ላይም የታመፀ መስሎኝ ነበር:: ይህ የሚያሳየን ንቅናቄው የኢህአዴግን መንገድ ሳይሆን የሚታገለው የኢህአዴግን መንገድ በተሳሳተ መንገዱ የሚያስፈፅሙትን ሰዎች ነው ማለት ነው:: ከዚህ አንፃር እና በተለያዩ የአንዳርጋቸው እና የብርሀኑ ፅሁፎች ተደጋግሞ እንደሚጠቀሰው ትግሉ ያነጣጠረው መለስ ዜናዊ ; በረከት ስምኦን ; ስብሀት ነጋ እና ጥቂት ቱባ ባለስልጣን እና ቱባ ስልጣን ያላቸው ካድሬዎች ላይ ነው ማለት ነው::

ገፅ 10 ላይ ደግሞም

> *<በሀገሪቱ በዘውግ አደረጃጀት ይሁን በዘውገ-ብዙነት ተደራጅተው የአመፅ ትግል ከሚያደርጉ ድርጅቶች ጋር በህብረት መስራትና እነዚህን የአመፅ እንቅስቃሴዎች የአጠቃላዩ የሀገራችን የፖለቲካ ቀውስ አጠቃላይ የመፍትሄ አካላት እንዲሆኑ ካለን ፍላጎት በመነሳት 1ኛ በመርህ ደረጃ አመፅን ያገለለ አካሄድ ብቻ የሚል አቋም በግንኙነታችን ላይ ሊፈጥረው ስለሚችል ችግር ሁለተኛ ግንቦት 7 ያስቀመጠውን የፖለቲካ ፕሮግራም ለማስፈፀም ከሌሎችም ሀይሎች ጋር በሚፈጥረው ህብረት ውስጥ የሚደረስበት ስምምነት በጉልበተኞች የሚቀማበትን; ከሀይል መበላለጥ እድል ክፍት አድርጎ ላለመሄድ በማሰብ.....>*

ይህ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳየን ከቀስተደመና መነሻነት እስከ ቅንጅት መመስረት ቀጥሎም እስከ ግንቦት 7 ምስረታ ውስጥ የታየውን ጊዜያዊ ጥቅም ያገናዘበ የትግል ስልት እና ፖለቲካዊ አድርባይነት የተጠናወተው አካሄድ ግንቦት 7 የተጠናወተው ነው::

በዘውጌ ከተደራጁት ውስጥ ደግሞም በትጥቅ ትግል እየተራመዱ ካሉት ዋናኞቹ ኦነግ እና ኦብነግ ናቸው:: የሁለቱ ግንባሮች አላማ ቁልጭ ብሎ የተቀመጠ ነው:; ኦነግ ኦሮሚያን ከአቢሲኒያ ነፃ ማውጣት ኦብነግ ደግሞ ኦጋዴንን ነፃ መንግስት ማድረግ ሲበዛ ደግሞም የታላቋ ሶማሊያ አካል መሆን ነው:: እንዴትስ ብሎ ነው ኦሮሚያን ለማስገንጠል እና ኦጋዴንን ለመሸኘት አይደለም አሰብን የማስመለስ ሲበዛ ደግሞም ኤርትራን ከእናት ሀገርዋ ጋር ለማዋሀድ ፕሮግራም የያዘ ንቅናቄ ከተጠቀሱት ግንባሮች ጋር አንድ የሚያደርግ መንገድ ያለው:: ከግንባሮቹ ጋር አንድ ከሚያደርገው ነገሮች ይበልጥ ከኢህአዴግ ጋር አንድ የሚያደርገው ይበልጣል::

አራተኛው በመለስ ዜናዊ አይን ህጋዊ በማይባል በህገ-መንግስቱ ግን ህጋዊ ሊሆን ይችል የነበረን የመብት ጥያቄ (ገፅ 10 እና 11)

*<ሁለገብ የትግል ስልት>* የሚለው እንዲሁ ምስጢራዊ እና ረቀቅ ያለ እንደሆነ እንድንረዳው የተፈለግን ያስመስለዋል:: ኢህአዴግን እንዲህ አድርገን እንረታዋለን የትግል ስልታችንም በዚህ መንገድ ነው ብለን ከነገርነው ትግላችን አይሳካም የሚል እንድምታ ያለው ይህ ሀሳብ ልክ ጨለማ ውስጥ ሆኖ አድብቶ እና ጠብቆ ጠላቱን በመሳሪያ እንደሚያጠቃ አቅመ-ቢስ ሰው ያደርገዋል:: ጠላቴን እንዴት እንደምገጥመው ከነገርኩት ወይም ካወቀ ያሸንፈኛል ከሆነ አባባሉ በጠላቱ መበለጥ ያወቀው የግንቦት 7 ንቅናቄ የማይዳሰስ ነው ማለት ነው:: እንግዲህ ማንኛውም ጥቃት ጊዜ ይፈጃል እንጂ መታወቁ ስለማይቀር ያኔ ግንቦት 7 ወደ Plan B, Plan C, Plan Z, Plan ZA, እያለ ሊጓዝ ነው ማለት ነው::

## <u>አንዳርጋቸውም <ለማጠቃለል> እኔም ለማጠቃለል-ገፅ 11 እና 12</u>

ዘጠኝ ነጥቦች ተጠቅሰዋል:: ግሩም ትንታኔዎች ናቸው:: ከሞላ ጎደል በጭንቅላቴ የሚመላለሱ ናቸው:: ሆኖም ግን ዶክመንቶቹ የታሉ? እንዴት ማግኘት ይቻላል? ዶክመንቶቹ ካሉ ተወያይተንባቸው አሳማኝ ከሆኑ እናም አገርን በማይጎዳ መልኩ ግንቦት ሰባት እንደተፈጠረ የሚያስረዱ ከሆኑ የኔ አይነቱን ማሳመን አሳምነውም የግንቦት 7 አባል ማድረግ ይችላሉ::

አለበለዚያ ንቅናቄው የተሰማራበት የጦር ሜዳ ኢንተርኔት ትግሉም ስብሰባ እና ተቃውሞ ሰልፍ ነው ማለት ነው:: ይህ ደግሞም ብርሀኑ ነጋ ወደ አገሩ ላለመግባት ለህዝቡ ያቀረበው ምክንያታዊ ስልት ነው የሚለውን ልጋራ ነው::

አንዳርጋቸው በአቶ መለስ <መንገዱን ጨርቅ ያድርግላቸው> ስላልተባለ ግንቦት 7ን ጠንካራ እና ኢህአዴግን ያንቀጠቀጠ አድርጎ ቆጥሮታል:: መልሴ ምኑ ተነካና በሶስት ወር ምጥ ማስወረድ እንጂ ልጅ ስለማይሆን ለአስተያየቱም ራስንም ለመመዘን ጊዜው በጣም ልጅ ነው::

የተሻለ ፓርቲ እስኪመጣ የኢህአዴግ ደጋፊ የምሆነው የአድር ባይነት ስሜት ተጠናውቶኝ ወይም ከጠነከረው ጋር ለመሰለፍ ሳይሆን ይህ መንገድ ለኢትዮጵያ የሚበጅ ነው ብዬ ስለማምን ነው:: ኢህአዴግ እስኪወድቅልኝ ቁጭ ብዬ ከምጠብቅ እና ኢህአዴግ እንዲወድቅልኝ አገሬን የሚጎዳ ዘለቄታዊ መዘዝ የሚመዝ እጅ እንዲኖረኝ አልፈልግም::

አንድ ፀሀፊ እንዳሉት እዚህ በባእድ አገር ለእንጀራዬ ብዬ እስኪያልፍ ያለፉል ብዬ የአለቃዬ የሚመር ባህሪን እየተጋቱ ፊቱም እየገረፈኝ እንደምስራው ለአገሬም ኢህአዴግን እስከነድክመቱ ብቀበለው እና ለአገሬ የሚጠቅም ነገር ማድረጉ የተሻለ ነው ብዬ ስለማምን ነው::

http://ethiomedia.com/all/law_peaceful.pdf

branaethio@yahoo.com